# ጠቢቡ ሰለሞን፣ ጥበበ የሱስን ተመስሎ መጣ እንዴ?

“ስለ አማርኛ ቋንቋ ቃላት በማንሳት መከራከር … ከኔ ይራቅ… ስለ ሃይማኖት ያነሳሃውን ግን በግዴለሽነት፣ በማናለብኝነት፣ …” ከሚል ቀረርቶ ጋር ጥበበ የሱስ የሰበቁብኝ ጦር… ጭቃ የማይወጋ… ቄጠማ ኖሯል።

በከበደ ሚካኤል ግጥም እንጀምር። ፍቺው እርስዎ እንዳሉት፣ ያ መሆኑን (በኮሚኒዝም ስም ያለቀው፣ ሃይማኖት የለሾችን ሃይማኖቴን ክጃለሁ ብላችሁ…” ለሚሉት ምንጭዎትን ባይጠቅሱልኝም[1] እርስዎ ባሉት መንገድ ሊፈታ እንደማይችል እንዲህ አስረዳለሁ።

> *“ጽድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም*
> *ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም”* በሚለው መንቶ ውስጥ፣ ሁለት መልእክቶች ናቸው ያሉት—ቢኖርም’ እና ‘ባይኖርም’ በሚሉት ቃላት ውስጥ።

1) ‘ቢኖርም’ የሚለው “ጽድቅና ኩነኔ ‘አለ’፣ ስለዚህ ከክፋት ይልቅ ደግነት ይሻላል ማለታቸው ነው ብለን እናስብ። ክፉ የሰራ ሰው እንደሚኮነን፣ ደግ የሰራ ደግሞ ጽድቅ ለመሆኑ ላለፉት በርካታ ሽህ አመታት በየሃይማኖቱ ሲነገር የኖረውን፣ ከበደ ሚካኤል አሁንም መልሰው የሚነግሩን አይመስለኝም። እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ግጥሙ እንዲህ ዝነኛ አይሆንም ነበር።
2) ‘ባይኖርም’ የሚለው “ጽድቅና ኩነኔ ‘የለም’፤ ስለዚህ ከክፋት ይልቅ ደግነት ይሻላል” ማለታቸው ነው ብለን እናስብ። ክፉ የሰራ ሰው፣ መጨረሻው መኮነን (ኩነኔ) ለመሆኑ፣ ጥሩ የሰራ ደግሞ ጽድቅ መሆኑ አይታወቅም። ከክፋት ግን ደግነት ይሻላል’ ያሉ ነው የሚመስለኝ።

ለማንኛውም መልእክቱ ከክፋት ደግነት የመሻሉን አስፈላጊነት መናገራቸው መሆኑን ከተስማማን ዋናው ይኸው ይመስለኛል። ወዳጄ ሆይ! ጥሩ እንስራ! የደስታ ሁሉ መሰረቱ ጥሩ መስራት ነውና! ጥሩ መናገር እንኳን ባንችል መጥፎ አንናገር። በህይወት ያለን ሰው “በቁም የሞተ” http://www.quatero.net/pdf/tsidqina%20kunenne.pdf ማለት ደግሞ መጥፎ ነው። ጥበበ የሱስ የሚለው ስምዎ እንዲያው ነው። ‘መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ’ አይነት። ጥበብን እንኳን አልታደሉም። “በቁሙ የሞተ” ያለችው የትኛዋ ቤተስኪያን እንደሆነች፣ ገጡን ይጥቀሱልኝና ያሳውቁኝ። ያኔ መልሱን ይዤ እቀርባለሁ። እርስዎ ራስዎ ያሉት ከሆነ ደግሞ ለኔ ለራሴ “ተሳስቻለሁ” ለማለት የሞራል ድፍረት ሊኖርዎት ይገባል። የሚደፍሩ ግን አይመስለኝም። ይህ የርስዎ ብቻ ችግርም አይደለም። ምክንያቱ ደግሞ፣ እንኳንስ ይችን ተራ

---

[1] ግጥሙን የያዘው መጽሃፍ የታተመበትን ዘመን መጥቀስ ያስፈልጋል። ተማሪ ፍስሃ ጋር መቸም መዳረቅ ነው የሆነብኝ። አንዱንም ጽሁፍ በማስረጃ ሊደግፍ አልቻለም። መልስ የተሰጠባቸውን ነጥቦች ሁሉ እንደገና እንዳዲስ እያነሳ ነበር የሚጽፈው። ለምሳሌ ዲባቶ መስፍን “ሳይንቲስት”ን “ሰገለኛ” በሚል የተካበትን ምክንያት ለማስረዳት ያን ሁሉ ደክሜም፣ የ “ዶክተር” ቃሉ የመጣው ከላቲን መሆኑንና “መምህር” ማለት መሆኑን ነው ባለፈው ጽሁፉ የነገረን። ሁለተኛ ወደሱ አልመለስም። በዚህ አጋጣሚ ኮሚኒዝምን ከሃይማኖት የለሽነት ጋር በማጣመር ማስፈራሪያ ‘እንኮኮ/እንጉጉ’ ማድረግ ስህተት ነው። ከቀዝቃዛው ጦርነት በፊትም ሆነ አሁን፣ የሃይማኖት የለሹ ብዛት ከምስራቁ ይልቅ በምእራቡ አለም ከፍተኛ ነበር። አሁንም ነው። ይህን ጎልጎሎ ማየት ይቻላል።

ስድብ፣ ሌላም ከባድ ደረቅ ወንጀል ቢሰሩ "ፍታት"፣ "ንስሃ" እና/ወይም "ጥፋትን ለነፍስ አባት (እግዜር) ብቻ መናዘዝ" የመሳሰሉት ስላሉልዎት፣ እኔን በቀጥታ "ይቅርታ" እንደማይሉ አውቃለሁና ነው። በግለሰብና በማህበረሰብ ውስጥ ይህ ጉዳይ ያለውን አሉታዊና አዎንታዊ ድርሻ በ"አብሄር (እግዜር) ተፈተነ" መጽሃፌ ላይ በዝርዝር የምገባበት ይሆናል።

ጥበበ የሱስ በእለተ እሁድ 29 Aug 2010 ለአንድ ድረ-ገጽ *[እስካሁን ታትሞ የወጣ አይመስለኝም፣ አለመውጣቱም አይገርመኝም]* እና ለኔም በግልባጭ በላኩት ጾዳቤ (እሜይል) እኔን "... የፈጣሪውን ስም ለመጥራት ጊዜ ከማጣቱ የተነሳ፣ ማይክሮ ሰከንዶችን ለመቆጣጠር ይዳዳዋል፣ ...ከኢትዮጵያዊ ጨዋነት ጋር የማይተዋወቅ፣... ኢትዮጵያዊ ነው ብሎ መገመት ያስቸግራል፣... ሰርጎ ገብ ወይም ቅጥረኛ ሊሆን ይችላል፣ የመንፈስ አባቱን ዳርዊንን አነሳ... ዝንጀሮ የዝንጀሮ ልጅ ሲሉት 'አቤት ጌቶቼ እያለ ጭራውን ያወዛውዛል፣ ሃፍረተቢስ!" ያሉኝ ሁሉ አልገረመኝም። የገረመችኝ 'አሰዳቢ' ብለው እኔኑ መልሰው የተሳደቡባት ቃል ናት። ይችን "አሰዳቢ" የምትል ቃል የማውቃት፣ ድክ ድክ የሚል ያምስት አመት ገደማ ትንሽ ልጅ ሆኜ፣ አያቴ ተጎረቤታችን ታያ ከልክሌ ቤት ይዘውኝ ሄደው፣ አዋቂዎቹ ከሚበሉት ማድ ታልበላሁ ብዬ ባለቅስ፣ አያቴ ወደ ቤት ስንመለስ ጠብቀው "መጥሃፉ 'እናት አባትህን፣ ታላቅህን አክብር' ይላል! ደሞ ልጅ ታዋቂ ጋር አይበላም!" አላልኩህም?' ብለው እስታሁንም ጠባሳው ባልጠፋ ቁንጥጫ እያበገኑኝ፣ ቆይተው "አሰዳቢ!" ያሉኝን ነው ያስታወሱኝ—አቶ ጥበበ/የሱስ ኅይለ/የሱስ። እዝጊዎ! ጊዜ እንዲህ ይሮጣል እንዴ! ስንት አመት አለፈው! 60ውን አጋመስኩት። አይ እድሜ ዘልዛላው—በስንት አመቴ ሰማሁት!

&&&&&&&&&&&&&

ነገርን ነገር ያመጣዋል መቸም። እውነተኛ ታሪክ ነው። አሁን በያ ሰሞን፣ ታንዱ ያማሪካ ጠቅላይ ግዛት እንዲህ ሆነ አሉ፡-

> እጣኑ ማሙሽ አማሪካን አገር በገባ በወራት ውስጥ አስኮላ ገብቶ ሲማር፣ አስተማሪ ክፍል ውስጥ ወዲያ ወዲህ እያለች፣ እያስረዳች እጇን ስታወራጭ ድንገት በማሙሽ አጠገብ ስታልፍ፣ ትንሹ ማሙሽ፣ አውላላ ሜዳ ላይ ድንገት ጭልፊት እንደመጣባት ጫጩት ደንግጦ፣ በስጋት ወደ ላይ አንጋጦ ጎንበስ ሲል፣ አስተማሪዋ ጋር ግጥምጥም! አስተማሪ በተራዋ ደንግጣ፣ ተገርማም "ምነው ማሙሽ? ምን ሆንክ? ..." ብላ ጠየቀችው። "...አባቴ ሁሌ 'እናትና አባትህን አክበር! 'ባለጌ!' እያለ ስለሚገርፈኝ ፈርቼ ነው" ይላል። አስተማሪ ለፖሊስ ንግር! ፖሊስ መልሶ ለፍርድ ቤት ንግር! ፍርድ ቤት ለማሙሽ ወላጆች የወላጅነት/አሳዳጊነት (parenting?) ትምህርት እንዲሰጥ፣ ቤት ውስጥ ደሞ የሚቀርጽ ካሜራ/video camera' እንዲገጠምም አዝዘው፣ ማሙሽን ሁለተኛ ድርሽ እንዳይሉበት አስጠንቅቆ ለቀቃቸው።

ታሪኩን በሰማሁ ሰሞን፣ "ዘይገርም..." እያልኩ፣ ስደመም ነበር የከረምኩት።... እንደ ማሙሽ ሳይገረፍ ያደገ ስንቱ ነው? እኔ እንኳን እድሜ ለጥበበ የሱስ "አሰዳቢ" በሚል ስድባቸው አስታወሱኝ። ... ይህ አስተዳደጋችን፣ ባህላችንስ ያሁኑን ማንነታችን ይናገር ይሆን? የሞራል እሴቶች መሰረት ሆኖ የቆየው ሃይማኖትስ? እናት አባትህን፣ ታላቅህን አክበር የሚል እንዳለ አስታውሳለሁ። ውላጅና ታላቅን ማክበር አግባብ ነው። በተለይ ልጆችና ታናናሾች ብዙም

በማይከበሩበት በኛው ማህበረሰብ ውስጥ… ይሄ ነገር…ሙሴ እንደሁ አሁን አይገኝ!… 10ቱ ትዛዛትን ሰርስመን (ኤዲት አድርገን) 'እናትና አባትህን አክብር' ተሚለው ላይ 'እንዲሁም ልጆችን እና ታናሾችንም አክብር' የሚል ቢገባስ? አለዚያም 11ኛ አድርጎ… አይ የኔ ነገር! አያርመኝ መቸም! ጥበበ የሱስ እንዳላስጠነቀቁኝ፡- "… ፈጣሪ አምላክ… በፍጥረቱ እንደሚታወቅ ልብ ማለቱ ይበቃሃል… ብዙ አትፈላሰፍ… ጠቢቡ ሰለሞን እንደተናገረ ጥበብ ፍልስፍና ማብዛት ትካዜ ማብዛት ነውና"። *ምንጭ፣ (አቶ?) ጥበበ የሱስ "ይድረስ ለኢትዮጵያዊያን በሙሉ!" በሚል በአጽንኦት፣ ከጻፉት የተወሰደ።*

ጠቢቡ ሰለሞን የምር እንዴት ጥበበኛ ኖሯል? የራሱን ጊዜ ሲጠበብ ኖሮ፣ ዛሬ በ21ኛው ክፍለ ዘመን፣ የኛኑ ጥበበኛ (አቶ?)ጥበበ እየሱስን ተመስሎ በመንፈስ መጥቶ፣ ዛሬም 'አትጠበቡ' ቢል … "ዘይገርም"! ተማለት በላይ ምን ይባላል? ተጥበበ የሱስ ጥሁፍ ውስጥ ምን ያልታየ ጥበብ አለ? ዘረፋም ያውቃሉ—ቅኔ ዘርፋ! 'ስለ ሃይማኖት ከመመራመር ጄት እንስራ' ለማለት ነው እንዲህ የተቀኙት "… እንዴት ብለን ነው ይህን ጄት እራሳችን አምርተን እግዚአብሄር ይሰውረንና፣ አንድ ቀን ነገረኛ ጭልፊት (ነ.ጭ.) ሲመጣ እራሳችንን የምንከላከለው?…" አሉ? መቸም 'ይችን የተማሩባት ቤተ-ቅኔ ዋሸራ ማርያም ናት? ወይስ መርጦለማርያም?' ብዬ የጅል ጥያቄም አልጠይቅ። ይልቅየ ወዲህ 'አትጠበቡ' እያሉ ወዲያ ደግሞ 'ጄት ይምጣልኝ' ብለው የጣፉትን ሳነብ፣ እኝህ ሰው ቅኔና መቋሚያቸውን ጥለው "ታቲር ሰሪ (ኮሜዲያን) ቢሆኑስ" ነው ያልኩ! ቂ…ቂ…ቂ…ቂ…ቂ….

የሰው ልጅ በጥበብና ፍልስፍና ሩጫ ላይ ነው—ፍጥነቱ ቢለያይም—አንዳንዱ በጥበቡና ፍልስፍናው ምጥቀት የተነሳ፣ ይኸኛውን አለም ለኛ ላዝጋሚዎቹ—(አትጠበቡ አትፈላሰፉ ለምንባለው—ራሳቸውም ለሚሉን—ለኛ) ጥለውልን—እነሱ ወደ ***ሌላው አለም*** ሲሄዱ እስኪመስል ድረስ መጥቀዋል።

ሌላው፣ ጥበበ የሱስ "..በቅን ልቡናና ትህትና በብሩህ አእምሮ (የማረኩን እንደሚሉት "ኦፕን ማይንድ") http://www.quatero.net/pdf/tsidqina%20kunenne.pdf እንድትቀበለኝ በማለት ስላደረጉልኝ የትህትና ጥሪ አመሰግናለሁ። መቸም እዚህም ቅኔ ተቀኝተዋል መሰለኝ። "የማረኩን" ሲሉ በቅኔ 😄 'ነጮች' ለማለት ፈልገው ይመስለኛል። ቅኔው ይቆየንና፣ እኒህ የ'ማረኩዎት' የሰለጠኑ ህዝቦችን ማለትዎ ነውና፣ እነሱ የማረኩዎት ህዝቦች፣ እንደርስዎ "… አትፈላሰፉ፣ አትጠበቡ፣ አትመራመሩ…" የሚል መዱስ (መ/ቅዱስ) ቢኖራቸውም፣ የሚፈላሰፉ፣ የሚጠበቡ እና የሚመራመሩ ፈጣሪ ሰዎቻቸውን ግን፣ ምናልባትም ከአብሄሩም (ከግዜሩም) በላይ *እያመለኩ* እና እያወደሱ ነው[2]! ወዳጄ ጥበበ የሱስ ሆይ! 'እግዚአብሄርን ለምን አብሄር አለ?' ብለው እዚሕ እርስዎ ይሟገታሉ። አረብ አገር ያሉ አረብ ክርስቲያኖች—ኦርቶዶክሶች—አምላካቸውን ሲያመሰግኑ "አላህ አክበር" የሚሉ ይመስለኛል። ግብጽ አገር

---

[2] 'ምስክር' የተባሉ ጸሃፊ፣ በኢትዮ ሚድያ "ክቡር ባህል" በሚል ርእስ በጻፉት እና "ይህንንስ ባህል እንዴት እናበረታታው" ብለው ባሳረጉት ጽሁፋቸው፣ ታላላቅ ስራ ሰርተው ያለፉትን፣ በህይወት ያሉትንም ዜጎቻችንን እውቅናን የመስጠቱን እና የማበረታታቱ ስራ፣ የአንድ ሃገር ልማት እድገትና ደህንነት ዋስትና መሆኑን እንደተናገሩልኝ እቆጥረዋለሁ! ይህን የሰዎችን ስራ እውቅና የመስጠቱን አስፈላጊነት፣ ባለፈው የግንቦት 7ትን መጽሃፍ በተቸሁበት ጽሁፌም ላይ ያነሳሁት ይመስለኛል። ሌላ ጊዜ በሰፊው የምመለስበት ቢሆንም፣ በዚህ አጋጣሚ፣ ይህ ታላቅ ስራ በስፋት ቢቀጥል ለአገራችንም ትንሳኤ ሲሆን ይታየኛልና፣ ይህንኑ እያዘጋጀ "ታላላቆቻችንን" እያወደሰልን ያለውን ታማኝ በየነን ሳላወድስ አላልፍም።

የተቀቡት የቀድሞዎቹ ጳጳሳት—የኛዎቹ—ሲማሩም ሲጸልዩም “አላህ አክበር” ሳይሉ ይቀራሉ? … መቼም ተተማሪ ፍስሃ እና ጥበበ የሱስ ኃይለ የሱስ ፊት Thank god! የሚል አማርኛ የሚያውቅ ሁሉ ዘንድሮ ወዮለት!😄

**ማሳረጊያ፡-**

ጥበብና ሃይሉን እየሱስ ያበዛልዎት “አቶ?” ጥበበ እየሱስ ሃይለ እየሱስ ሆይ! ትህትናዎ መቸም አለቅጥ በዛ። “… ሃሳቤን እንድትቀበል በታላቅ ትህትና **እለምንሃለሁ**” በማለት ራስዎን የስነ-ምግባር ቁንጮ አስመስለው “…እንደዚህ አይነት እምነት ያለውን ሰው፣ **ቤተ ክርስቲያን በቁሙ የሞተ ትለዋለች**” በማለት [http://www.quatero.net/pdf/tsidqina%20kunenne.pdf](http://www.quatero.net/pdf/tsidqina%20kunenne.pdf) ደግሞ ቤተስኪያኗን በስነ ምግባር እዚያ ታች አወረዷት። ትህትና ሲሆን ከእርስዎ ነው። ስድብ ሲሆን ደግሞ ከቤተስኪያኗ! መቸስ ቤተስኪያኗ በምትመራበት መጹስ (መ/ቅጹስ) ውስጥ እንዲህ ያለ ጸያፍ ጽሁፍ ያለ አይመስለኝምና፣ ይህን ነውረኛ አባባል የርስዎና የርስዎ ብቻ አድርጌ ነው የምወስደው። ታዲያ እርስዎ የሃይማኖቱ አስተማሪ/ሰባኪ ቢሆኑ (*‘ቢሆኑ’ ነው ያልኩ ልብ ይበሉ*)፣ “… ቤተ ክርስቲያን ባልሄድ፣ እንዲህ ያልተገራ አንደበት ካለዎት ሰው፣ ከእርስዎ ምን አገኛለሁ?” ብዬ እንዳይመስልዎት። የለም የለም። ምክንያቱ እሱ አይደለም—መልካም አንደበት ያላቸውም አሉና ነው። በየጃካ ሂርሳኮቹ (መገናኛ ብዙሃኑ)፣ ስለ ዲያቆን ቀሳውስቱ፣ ስለ ጳጳሳቱም የሚነገረውን፣ የሚጻፈውን የስነ-ምግባር ጉድለት፣ የሞራል ድቀቀት ስላነበብኩና፣ ከኔ የተሻለ የሞራል ብቃትና ስነ-ምግባር የሌለው ሰው የሚናገርውን ብሰማ አይጠቅመኝም ብዬም አይደለም። የለ የለም። ይኸም አይደለም—ከኔ የተሻለ የሞራል ብቃትና ስነ-ምግባር ያላቸውም አሉና። ምክንያቴ እንዲህ ነው። በደንብ ያዳምጡኝ። **እንደኔ ሰው የሆነ ሰው፣ እንደኔ የሚዳሰስ፣ የሚታይ፣ የሚሰማ** (*‘ሰ’ን ያጥብቁልኝ*)… **ሰው የሆነ ሰው፤ ስለ ሌላ የማይታይ፣ የማይዳሰስ፣ የማይሰማ** (*‘ሰ’ን ያጥብቁልኝ*) **አብሄር (እግዚአብሄር) የሚናገር ‘አዋቂ’ን ለመስማት ወደ ቤተሄር (ቤተስኪያን) ወይም ማንኛውም ሌላ ቤተ አምልኮ አልሄድም[3]። ምክንያቱም፣ የዚያ ‘አዋቂ’ እውቀት እንደማንኛውም**

---

[3] አንዳንድ ወዳጆቼ ‘ለሰዎቹ ብለህ አይደለም፣ ለቤተሄሩ (ቤተስኪያኑ) … ብለህ ነው መሄድ’ ይሉኛል። ሲለኝ በወራት፣ አንዳንዴም እስተ መንፈቅ እያሰለስኩ ቤተሄር (ቤተስኪያን) እሄዳለሁ። አብዛኛውን ጊዜ ግድግዳው ላይ ማፍጠጥ ነው የሚሆንብኝ *(እስቲ እንዲያው አሁን እኔን ይጠለይልኛል እንጂ ‘አሰዳቢ’ ‘በቁሙ የሞተ’ ልባል ይገባኛል? ለነገሩ ቢጸለይልኝስ እንደ ጥበበ የሱስ ኃይለ የሱስ ያለ፣ ራሳቸው ‘አሰዳቢ’ ብለው በሚሳደቡ ሰው፣ በእሳቸው ቢጠለይልኝ እግዜሩስ ይሰማል?)* አንዳንዴ ደ’ሞ እንዲያው እርር ብግን የሚያደርግ ስብከት ይገኜ እመለሳለሁ። አንዴ ባንዱ ቤተሄር እንዲህ ተሰበከ። *“…ላንተ የማደርግልህን አንድ ነገር፣ ለጠላትህ እጥፍ አደርጋለሁ። ምን ላድርግልህ? ተብሎ ቢጠየቅ ‘አንድ አይኔ ይጥፋ’ አለ አሉ። የጠላቱ ሁለት አይን እንዲጠፉ እኮ ነው! የሰውን ክፋት አያችሁ?…”* ብሎ ሲያበቃ *“ሰው እንዲህ ነው። ደግነት ከእግዚሃር ብቻ ነው። እዚሃርን ነው ማመን…”* በመሰለ አይነት ማሳረጊያ ነበር የዘጋው—ሰባኪው። አሁን ይቺ ተረት መጹስ (መ/ቅጹስ) ውስጥ አለች’ንዴ? ብትኖርስ ደሞ፣ ደግ ደጓንም ጥቅስ አዘውትረው ቢጠቅሱልን አይሻልም? እውን እንዲህ ክፋት የሚያስብና ምቀኛ ሰውስ አለ? ከቤተስኪያን ውጪም ቢሆን የምንሰማቸው እንደ “… አበሻ ምቀኛ ነው! አብሮ መብላት እንጂ አብሮ መስራት አይሆንለትም…” የመሳሰሉት እጅግ መርዘኛ አባባሎች ምንጫቸው የት ነው? ሰውን እርስ በርስ እንዳይተማመን በማድረግ ያላቸውን መጥፎ ጎን አይታችሁልኛል? ይህን የ“አበሻ ምቀኛ ነው” ከትውልድ ወደ ትውልድ… ሰንሰለት እንዴት እንበጥሰው? እኔ ሁለት ዘዴዎች አሉኝ። 1) ከልጆቻችን፣ ከታናሾቻችን ፊት ይኸን ጨርሶ አለማለት። 2) ‘አበሻ ምቀኛ ነው’ ለሚልህ ሰው መልሱ ‘እኔ አበሻ ነኝ። እኔን ምቀኛ ነው ካልከኝ፣ አንተ ራስህ ምቀኛ ነው ብለህ የምታስበኝን—እኔን—የምቀኛ ምቀኛ ሆነህ ላለመቅረብህ ምን

**የትምህርት ዘርፍ በመማር የሚገኝ እውቀት ስለሆነ ነው። ከሰማየ ሰማያት የወረደ/የተሰጠ እውቀት አይደለም። በትምህርት የተገኘ እውቀት ነው። ያ እውቀት/ትምህርት ደግሞ እኔ ልማረው የምመርጠው ዘርፍ አይደለም። አለቀ!**

ይህ የኔና የኔ እምነት ነው። በሌላ አባባል ‘ሰባኪነት ከሰማየ ሰማያት የተገኘ እውቀት ነው’ ብሎ የሚያምን ሰውን ‘ተሳስተሃል’ አልልም። ምን ቆርጦኝ? እንኳንስ ከማይታይና ከማይዳሰሰው ከአብሄር (እግዚአብሄር) የተገኘ ነው ስለተባለለት የሰባኪነት እውቀት ስጦታ/ችሎታ ይቅርና፣ ጧት ተቤታቸው ሲወጡ፣ በሰማየ ሰማያት የምትበር ወፍ ኩሷን ራሳቸው ላይ ብትጥልባቸው “ዛሬ ውሎየ ቀኝ በቀኝ ነው፣ የሲሳይ ቀን ነው” የሚሉኝን፣ ቀኑን በሞላ እንደሚቀናቸው እያሰቡ፣ እየተደሰቱ ለመዋል የተነሱትን ያያ ከልክሌን ደስታ፣ ለምን አስቀርባቸዋለሁ? ይህንንስ ‘ሎጂክ’ በምን ማስረጃ ነው ትክክል አለመሆኑን የምሞግተው? አይደለም የጋራችን በሆነችው አገራችንና፣ የዚያው መገለጫ በሆኑት እንደ ልማት፣ ትምህርት፣ ቋንቋ (ለምሳሌ እንደ ዲባቶ መስፍን ለንግሊዝና ሌሎችም መሰል ቃላት አዳዲስ ቃላት መፍጠር) ወዘተ… ቀርቶ፣ እንደ አያ ከልክሌ ‘አጉል’ የሚባል የግለ-ሰብ አምልኮ/እምነት ጉዳይ ቢሆንም እንኳን፣ ይህን ያህል ርቆ በመሄድ፣ የግለ-ሰብን አስተሳሰብ/መብት ማክበርና መከባበር፣ ጥሩና መጥፎ በምንላቸው ባህሎቻችን፣ ልማዶቻችን፣ ልምዶቻችን፣ ሃይማኖትንም እንኳን ቢሆን፣ ወዘተ… ስንነጋገርም መቻቻል፣ በተገቢ ቋንቋ መነጋገር ያስፈልጋል። ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ በሃይማኖት ላይ በመንጠልጠል እና ሃይማኖትን ከለላ አድርጎ፣ የፈጠራ ስራን እና/ወይም ሰሪዎችን መኮርኮም ይበቃ!

&&&&&&&&&&&&&&&&&

Gelanew-kirar@hotmail.com

---

ማረጋገጫ አለኝ? ስለዚህ እንዲህ አይነት ጅምላ (ጄንራላይዜሽን) ወቀሳ፣ ተቀባይነት የለውም” ብሎ ካለ ይሉኝታ መንገር።

ሌላው ቤተሄር መሄድ የማይመቸኝ፣ ግድግዳው ላይ ማፍጠጥ… የለ የለም። የፈረንጅ እዚሃር፣ ማርያምና ጎርጊስ ጋር መፋጠጥ ነው እንጂ።… ባይሆን የሰውን ዘር እኩል የሚውክል ቀለም ያለው እግዜር፣ ማርያም፣ ጎርጊስ ሚኪያል… ምስል ሲሰራ፣ ያኔ አዘወትር ይሆናል። እሚገርመኝ ነገር… አብሄር፣ ማርያምንና ሌሎችንም አማልክት በፈረንጅ አምሳል (ነጮች አድርጎ) መሳል (ስእል) መቼ ተጀመረ? ሰይጣንንስ ማነው ጥቁር አድርጎ የሳለ? … ከስእሎቹ መፈጠር በፊት የሰው ልጅ የውበት መስፈርቶች ምን ምን ነበሩ? እግዚሃርን ማርያምንና አማልክቶቹን፣ ነጭ፣ ሰልካካ አፍንጫ፣ ጠጉረ ላሁጫ፣ ወዘተ፤ ሰይጣንን ደግሞ ጠቋራ፣ ሲሻቸው ጠጉረ ከርዳዳ፣ ሲመቻቸው አፍንጫ ጎራዳ፣ አንዳንዴም ከንፈረ ከባዳ… ወዘተ አድርገው መሳል ከጀመሩ ወዲህ ሳይሆን ይቀራል—የውበት መስፈርት የተጀመረው? አይ የኔ ነገር! እርጅና ነው መሰለኝ! መርሳት አበዛሁ!….ጥበበ የሱስ ‘አትመራመር’ ‘አትፈላሰፍ’ ብለው ነበር—ጠቢቡ ሰለሞንን ተመስለው! ይኸ ፍልስምና ቢበቃኝስ እናቴ! ሆ…! ቸር ይግጠመን!